# አንታይ ቫይረስ ያሻል

ባንድ ወቅት ፣ ከወያኔ ፣ ስልጣን የተጋሩ
ባለ ጊዜ ሆነው ፣ ጮቤ የጨፈሩ
በጭካኔ ህዝብን ፣ ካገር ያባረሩ
ጠባብ ወንጀለኞች ፣ ዘር የመነጠሩ
ሰው ከነ ህይወቱ ፣ ገደል የጨመሩ
በምን ሂሳብ ፣ ዛሬ ፣ ይባሉ እሹሩሩ
ንሰሃ ሳይገቡ ፣ ከወንጀል ሳይጠሩ ?

ትላንት ያሳፈረን ፣ የሕዝብ ትግል ገሎ
አድብቶ የኖረ ፣ ሊሄድ ተገንጥሎ
ሺዎችን የፈጀ ፣ ከገደል ላይ ጥሎ
ቁንጫና ቅማል ፣ ቱካን ተግተልትሎ
ቅንቅን ላይ ሊዘመት ፣ ማን ከማን ፣ ተሽሎ
የበታኞች ቡፌ ፣ ስልቻን ቀልቀሎ ።

ለጥፋት ለውድመት ፣ ካልሆነ መልከስከስ
ማልዌር ፣ ቱሮጃን ሆርስ ፣ መሰብሰቡ ቫይረስ
ሲገነባ አላየን ፣ ካልሆነ ለማፍረስ
ሁሉን እንዳይመርዝ ፣ ሁሉን እንዳያረክስ
በኖርተን ማካፌ ፣ መረሸን መከስከስ
ሞቱን ማረጋገጥ ፣ ዳግም ላይመለስ
ከትግላችን ደጃፍ ፣ አጠገቡ እንዳይደርስ ።

ባንድነት ሰበካ ፣ ህሊናን አፍዝዞ
ነቀዝና መዥገር ፣ የሚጓዝ አርግዞ
እከክ እንዳይሆንህ ፣ ገላህን መርዞ
ደምክን እንዳይመጠው ፣ ከስርህ መዝምዞ
ለቁንጫ ቱካን ፣ ላይሶል ፣ ፍሊት ገዝቶ
ዲኘ ዲዲቲውን ፣ በመንገዱ ረጭቶ
ያስፈልጋል ጉዞ ፣ በትጥቅ ተደራጅቶ ።

ማፍረስ በተካነ ፣ በጎጠኞች ቅጥር
ስልጣን የተጠማ ፣ ጎጠኛ ሲያፈቅር
ተገንጣዩን አዝሎ ፣ ትግል እንዳይቀብር
ሲተራመስ ውሎ ፣ ሲተራመስ ቢያድር
መዘናጋት የለም ፣ ባንድነት ግርግር
አንታይ ቫይረስ ያሻል ፣ ትግል እንዲሰምር ።

ታዛቢው ... May 15, 2011